# ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ

Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

efdpu@aol.com www. Finote.org

**ፕሮግራም፦** ረቡዕና እሁድ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት አስከ ሶሰት ሰዓት በ 25 ሜትር ባንድ

**Program**: Wednesday and Sunday 8:00PM- 9:00 PM on 25 meter band.


## ዜና ዘገባ

***መጋቢት 16 ቀን 2005 ዓ.ሞ.***

***ህወሀት 9 የማዕከላዊ ኮሚቲ አባሎችን አሰናበተ፤***

***ኦህዴድ 3 አንጋፋ ባለስልጣናቱን ከስራ አስፈጻሚነት አባረረ፤***

***ለግራዚያኒ ያዘነው የወያኔ ቡድን ከ40 በላይ ዜጎችን በግፍ አስሮ አደረ፤***

***ሙስሊሙ በናዝሬት/አዳማና በሻሸመኔ ተቃውሞውን አስተጋባ-***

***ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ታፍሰው ታሰሩ፤***

*የወያኔ ከፍተኛ ባለስልጣናት ከበረሀ ጀምሮ ይዘውት የመጡትን ጥሎ ማለፍ ስልት በአሁኑ ሰዓትም ተግባራዊ ለማድረግ በቡድን ተከፋፍለው እርስ በርስ እየተፋለሙ መሆናቸውን አንድ የወያኔ ማዕከላዊ ኮሚቲ አባል አጋለጠ።*

*የወያኔ 11ኛ ጠቅላላ ጉባኤ መቀሌ ከተማ ላይ ለማድረግ ከቻይና እስከ አሜሪካ.....ከእንግሊዝ እስከ ዱባይ......ከደቡብ አፍሪካ እስከ ሱዳን ድረስ ያሉ ከፍተኛ አመራሮች ከያሉበት ተሰብስበው የተገኙ ቢሆንም በድርጅቱ ውሰጥ የተፈጠረው ክፍፍል በግልጽ የታየበት እና አንደኛው ወገን አይሎ የወጣበት መድረክ እንደነበር በስፍራው ከነበሩ ወገኖች የደረሰን ጥቆማ ገለጸ።*

*ጉባኤው ሊደረግ ከነበረበት ግዜ በወራት ያህል ያራዘመው የወያኔ ቡድን በውስጡ የተፈጠረውን ሽኩቻና የእርስ በርስ ክፍፍል እልባት ለመስጠት በሚል አራዝሞ የቆየ ሲሆን ሰሞኑን በመቀሌ ባደረገው በዚሁ ጉባኤ ላይ የተባረሩ የቀድሞ አመራሮች ይመለሱ ብለው ይፎክሩ የነበሩት ክፉኛ ተበልጠው የታዩበት መድረክ እንደነበረም የደረሰን ጥቆማ አጋልጦዋል።*

*እሁድ መጋቢት 8 ቀን 2005 ዓ.ም ሕወሀት በመቀሌ 11ኛውን .....ኢህዴን /ብአዴን በባህርዳር 10ኛውን .....ኦህዴድ በአዳማ 7ኛውን .....ደኢህዴን ደግሞ 8ኛውን በአዋሳ ጉባኤያቸውን መጀመራቸው ታውመቂ። ሕወሀት በዕለቱ የመለስን ዘላለማዊነት ለማንገስና እና ፍጹም መልአክ*

አስመስለው ለማቅረብ የተደረገው ዝግጅት የሰማዕታት አዳራሽ ብለው በሚጠሩት ሰፍራ የተከሄደ ሲሆን ለተገኙት የወያኔ አመራሮች ሰፊ ፕሮፓጋንዳ ከተነዛላቸው በሁዋላ የተፈራው ጭቅጭቅ እና ንትርክ አቅጣጫ እንዲቀይር የተደረገ መሆኑ ታውቀዋል:: የእነ አባይ ወልዱ ቡድን ደጋፊ የሆነው ቲዎድሮስ ሐጎስ የተሰኘው ግለሰብ የመድረክ መሪነቱን በመያዝ ሌሎቹን ሊቆጣጠር እንደቻለም ከስፍራው የደረሰን ጥቆማ ገልጸዋል::

በወያኔ አመራር መሀከል ክፍፍል መኖሩን ያመነው የድርጅቱ ማዕከላዊ ኮሚቲ አባል የሆነው ብርሀነ ኪዳነማርያም በወያኔ ውስጥ የተፈጠረው ክፍፍል አዲስ እንዳልሆነና ከጫካ ጀምሮ አብሮ የመጣ መሆኑን ጠቅሶ አሁንም ችግሩ መኖሩንና በቅርቡ የሚቀረፍ መሆኑን መግለጹ እስከ ዛሬ ሲናፈስ የነበረውን ወሬ እውነት መሆኑን አረጋግጦዋል::

የክፍፍሉ መንስኤ ምን እንደሆነ ለግዜው ከመግለጽ የተቆጠበው ይሄው የማዕከላዊ ኮሚቲ አባሉ ብርሀነ ኪዳነማርያም በአመራሩ መሀከል ችግር መኖሩንና ክፍፍሉ እንዳለ ጠቅሶ ይሄ እንደ አዲስ የሚነሳ አጀንዳ ሳይሆን ከዚህ በፊትም በረሀ ላይ እነ አረጋዊ በርሄ እና እነ ግደይ ዘርዐፅዮን በነበሩበት ግዜ ተመሳሳይ ችግር ተፈጥሮ የእነ አቦይ ስብሀት ነጋ ቡድን አሸናፊ ሆኖ የወጣበት እንደነበር፤ በ1993 ዓ.ም በመለስ እና በስዬ ቡድን መሀከል ተመሳሳይ ችግር ተፈጥሮ መለስ አሸናፊ ሆኖ የወጣበትን ማስታወሱ በቂ ነው ካለ በሁዋላ በአሁኑ ሰዓት የተፈጠረው ክፍፍል ግን በውይይት እና በመነጋገር ሊፈታ የሚችል መሆኑን ገልጸዋል::

በምስጢር ታፍኖ ለብዙ ግዜ ተይዞ የነበረው የህወሀት ክፍፍል በ11ኛው ጉባኤ ላይ በግልጽ ወጥቶ የመነጋገሪያ ርዕስ ሆኖ የሰነበተ ሲሆን የእነ አባይ ወልዱ ቡድን ግን የበላይነቱን ያስመሰከረበት ነው ተብሎዋል::

ህወሀትን መለስ ቀብሮት ነው የሄደው ስለዚህ የተወገዱ የህወሀት ባለስልጣናት ወደ ድርጅቱ እንዲመለሱና ትንሳኤውን እንዲያሳዩን በሚል ሰፊ ቅስቀሳ ሲያደርግ የነበረው ስብሀት ነጋ እየተሸነፈ ከመምጣቱም በተጨማሪ በጉባኤው ላይ ሳይገኝ መቅረቱም ታውቆዋል::

እነ ስብሀት ነጋ የታችኛውን አመራር በተለያዩ ስልቶች መያዛቸውን ያረጋገጠው የአባይ ወልዱ ቡድን በበኩሉ የጦር ክፍል አዛዦች እየተዘዋወረ በማግባባት እና በመለስ አጥንት እያለ እየተማጸነ ወደ ራሱ ቡድን የቀላቀላቸው ከመሆኑም በላይ እነ ስብሀትን የህወሀት አፍራሽ አድርጎ በማቅረቡ ሰፊ ድጋፍ ከጦሩ አዛዦች ሊያገኝ እንደቻለም ለማወቅ ተችሎዋል::

የሰሜን እዝ ዋና አዛዥ የሆነው ሳዓረ መኮንን ከአባይ ወልዱ ጋር በመሆን በእዙ ስር ያሉትን የጦር አዛዥ የህወሀት ሰዎች በሙሉ እያሳመነ ለቡድኑ እንዲወግኑ ከማድረጉም ባሻገር የእነ ስብሀት ነጋ ቡድን ሕወሀትን አዳክሞ ለሌላ አሳልፎ ሊሰጥ በመሆኑ ለሁላችንም የህልውና ጥያቄ ነው በማለትም ሰፊ ቅስቀሳ ሲያደርግ እንደነበርም የደረሰን ጥቆማ አስረድቶዋል::

በዚሁ መቀሌ ከተማ በተደረገው 11ኛ ጉባኤ ላይ ከውጭ ሀገር የመጡ የድርጅቱ ነባር ሰዎች የተገኙ መሆናቸው ታውቋል:: በቻይና ሀገር በአምባሳደርነት እየሰራ የሚገኘው የቀድሞው የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ስዩም መስፍንም የሽምግልና ስራውን አጠናክሮ ቢገፋበትም በማዕከላዊና በስራ

አስፈጻሚ ኮሚቴ ምርጫ ላይ ከፍተኛ ሙግት እና ትግል ገጥሞት እንደነበርም የደረሰን ጥቆማ ገልጾዋል፡፡

መተካካት የሚለውን መለስ የጀመረውን ነባር ተቀናቃኝ ባለስልጣናትን የማባረሪያ ስልት በመጠቀም የእነ አባይ ወልዱ ቡድን ሰሞኑን በተደረገው ጉባኤ ላይ ከእነ ስብሀት ጋር የወገነውን እና ከመለስ ጋር ሆድና ጀርባ የነበረውን አርከበ እቁባይንና መሀል ሰፋሪ ሆኖ ሳይወስን ግራ ተጋብቶ የቆየውን ምክትል የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ብርሀነ ገብረ ክርስቶስን እንዲሁም ሽምግልና ይዞ ላይ ታች ሲል የነበረውን ስዩም መስፍንን ፤ ጠንካራ ተሙዋጋች ነው የተባለው ዘርዐይ አስገዶምን ከማዕከላዊ ኮሚቴ እና ከስራ አስፈጻሚነታቸው ሙሉ ለሙሉ ያባረራቸው መሆኑም ታውቆዋል፡፡

ወያኔ ከማዕከላዊ ኮሚቴ አባልነት ያባረራቸውን ሰዎች የምስክር ወረቀት የሰጣቸው ሲሆን አርከበ እቁባይ ፤ብርሀነ ገብረክርስቶስ እና ዘርአጽን አስገዶም አኩርፈው በፕሮግራሙ ባለመገኘታቸው በስራ ምክንያት አልተገኙም በማለት ለተሰብሳቢዎቹ የተገለፀ ሲሆን ስዩም መስፍንን ጨምሮ መንግስተአብ ገ/ኪዳን፤መሰረት ገ/ማርያም፤ደስታ በዛብህ፤ይህሼ ለማ እና ንጉሴ ገብሬ ለተባሉት የመሰናበቻ ዝግጅት እንደተደረገላቸው ታውቆዋል፡፡

የእነ ስብሀት ነጋ ቡድን ስር ሰዶ በጉባኤው ላይ ብልጫ ለማምጣት ብርቱ ትግል አድርጎ የነበረ ቢሆንም በስዩም መስፍን ጣልቃ ገብነት እና ሽምጋይነት ነገሩ እንዲረግብ ተደርጎ የነበረ ቢሆንም ድንገት ሳይታሰብ መተካካት በሚለው ጠልፎ መጣያ ስልት የእነ አባይ ወልዱ ቡድን የበላይነትን አግኝቶ ዘጠኝ ሰዎችን ከማዕከላዊ ኮሚቴ አባልነት አንስቶ በሌሎች መተካቱን በይፋ መግለጹ ታውቆዋል፡፡

ሥዩም መስፍንን ,አርከበ እቁባይንና ...ብርሀነ ገብረክርስቶስን ከስራ ጫና መብዛት፤ ከጤና መታወክ ከድካም ጋር.....ሌሎቹን ከእረፍት ጋር በማያያዝ እንዲሰናበቱ የቀረበው ጥያቄ በጉባኤተኞች የጸደቀላቸው ሲሆን እነ አዜብ መስፍንና አባይ ወልዱ በተሰናበቱት ምትክ የራሳቸውን ሰዎች ለማስቀመጥ መቻላቸውን ለማወቅ ተችሎዋል፡፡

ወትሮም ከጫወታው ውጭ ሆኖ የነበረው ህመምተኛው ስዩም መስፍን ለራሱ ሳይሆን ለድርጅቱ ሕልውና ሲል ሁለቱን ቡድኖች ለማስማማት ብዙ ጥረት ሲያደርግ ቢቆይም ሳይሳካለት የቀረ ከመሆኑም በተጨማሪ ድንገት እራሱም ተሰናባች ሆኖ በመቅረቡና አርከበ እቁባይም ከማዕከላዊና ከስራ አስፈጻሚነት ቦታው መነሳቱን ተከትሎ የእነ ስብሀት ቡድን እጅግ መደናገጡን እነዚሁ ወገኖች ተናግረዋል፡፡

የወያኔ ጀሌዎች የሆኑት ሶስቱ ድርጅቶች በበኩላቸው በባህር ዳር..... በአዋሳና በአዳማ/ናዝሬት ከተሞች ጉባኤያቸውን ሲያደርጉ የሰነበቱ ሲሆን ባደረጉት ስብሰባዎች ላይ የማዕከላዊ ኮሚቴ እና የስራ አስፈጻሚ አባሎችን መርጠው ማቅረባቸው ታውቆዋል፡፡

በህዝብ ቁጥር ድልድል ይደረግ ተብሎ በተወሰነው መሰረት ኦህዴድ 81 የማዕከላዊ ኮሚቴ አባሎችንና 9 የስራ አስፈጻሚዎችን የመረጠ ሲሆን እንደ ወያኔ ሁሉ መተካካት በሚለው ስልት በመጠቀም ኩማ ደመቅሳን...ግርማ ብሩንና አባዱላ ገመዳን ከስራ አስፈጻሚነት ያባረራቸው ሲሆን በምትካቸውም ከማዕከላዊ ኮሚቴ አዳዲስ የተባሉ ካድሬዎች ተመርጠው ወደ ስራ አስፈጻሚነት መግባታቸው ታውቆዋል፡፡

ብአዴንም በበኩሉ 65 የማዕከላዊ ኮሚቴ እና 9 የስራ አስፈጻሚ መረጥኩ ብሎ ያስታወቀ ቢሆንም እጅግ አስገራሚው ነገር በ2003 ዓ.ም በአዳማ በተደረገው ጉባኤ ላይ መተካካት ተብሎ በጡረታ የተሰናበተው አዲሱ ለገሰ ተመልሶ የብአዴን የስራ አስፈጻሚ ሆኖ መምጣቱን ነው:: ደኢህዴን 55 የማዕከላዊ ኮሚቴና 9 የስራ አስፈጻሚ አባሎችን መርጦ ያቀረበ ሲሆን ነባር የስራ አስፈጻሚ ከነበሩት መሀከል ሁለቱን ማለትም ታገሰ ጫፎንና ደበበ አበራን አባርሮ በምትካቸው ደሴ ዳልኬንና ተስፋዬ ባልጅግ የተባሉትን መተካቱ ታውቆዋል::

ሕወሀትም 9 የማዕከላዊ ኮሚቴ አባሎችን አባርሮ በምትካቸው ሌሎችን መርጦ 45 የማዕከላዊ ኮሚቴና 9 የስራ አስፈጻሚ ለባህር ዳሩ ጉባኤ ማቅረቡን የደረሰን ጥቆማ ገልጾ በየድርጅቶቹ የተደረገው የመተካካት ስራ ቅዳሜ መጋቢት 14 ቀን 2005 ዓ.ም በባህርዳሩ ጉባኤ ላይም እንደሚቀጥል እየተነገረ ይገኛል::

በምስረታ ከኦህዴድ አናሳ የሆነው የእነ ኃይለማርያም ደሳለኝ ደኢህዴን 8ኛ ዓመታዊ ጉባኤ በሚል በአዋሳ ለሁለት ቀናት ብቻ ባደረገው የለብለብ ስብሰባ በጥልቀት እና በሰከነ መንገድ አንዳችም ውይይት ሳያደርግ ቀድሞ የነበሩትን ሰዎች መልሶ በመምረጥ ያጠናቀቀ ሲሆን ኦህዴድ በበኩሉ በውስጣዊ ችግሮቹ በተነሱ ጥያቄዎች መፍትሄ ሳያገኙ እርስ በርስ ሲነታረኩና ሲጎሻሽሙ ቢሰነብቱም በወያኔያዊ ጥበብ ነገሮች ሁሉ ባሉበት እንዲሆኑ ተደርጎ ስብሰባው መጠናቀቁ ታውቆዋል::

በሙት መንፈስ ሲመሩ የነበሩት የአራቱም የወያኔ አባል ድርጅቶች ቻይና ታትሞ በመጣ የመለስ ምስል የመሰብሰቢያ አዳራሾቻቸው አብረቅርቀው በሕወይወት ያለ እየመሰላቸው እየበረገጉ አሁንም አሁንም መልሰው መላልሰው የመለስን ራዕይ እናስፈጽማለን እያሉ እንደ ዳዊት ስሙን ሲደጋግሙት መክረማቸው ድርጅቱ አንድም በራሱ የሚተማመን ሰው እንደሌለው በግልጽ ያሳየበት ጉባኤ ነው ተብሎዋል::

በተለይ መለስ በሕይወት በነበረበት ወቅት ስብሰባ ሲመራ የሚቀመጥበት ወንበር ላይ ደፍሮ የሚቀመጥ ጠፍቶ በአካል እየመጣ የሚያያቸው እየመሰላቸው እነ አባይ ወልዱ አስሬ ወንበሩን እየገላመጡ እና እያዩ ስብሰባውን መጨረሳቸው በጉባኤተኞችም ጭምር ግራሞትን የጫረ ጉዳይ እንደነበረ ከስፍራው የደረሰን ጥቆማ አስረድቶዋል::

አራቱም ድርጅቶች ጉባኤያቸውን ለማድረግ በመቶ ሚሊዮን የሚቆጠር ብር ከመንግስት እና ከሕዝብ ካዝና ወጪ አድርገው የመለስን ምስል የያዘ ካኒቲራ..... ኮፍያ.....ከረቫት...ሸሚዝ....ኮት.....ከማሰራታቸውም ባሻገር ለእያንዳንዱ አባል የውሎ አበል በሚል በሺህዎች የሚቆጠር ብር የተሰጣቸው ከመሆኑ በላይ የሆቴል እና የምግብ እንዲሁም የትራንስፖርት ወጪም በተመሳሳይ ከፍተኛ እንደነበረም ጉዳዩን ሲከታተሉ የነበሩ ዜጎች ይናገራሉ::

በሌላ ዜና በአንድ ቀን ከ30 ሺህ በላይ ዜጎቻችንን እንደ ሳር ከምሮ ያቀጠለውን የፋሽት ኢጣሊያ ጦር አዛዥ የግራዚያኒ ሐውልት መሰራትን ለመቃወም በወጡ በነበሩ ታዋቂ ምሁራንና የተቃዋሚ ፓርቲ አመራሮች ላይ የእስራት እና የድብደባ ዘመቻ መካሄዱ ታወቀ::

*እሁድ መጋቢት 8 ቀን 2005 ዓ.ም ከጠዋቱ 3:30 ላይ የፋሽሽቱ ኢጣሊያ ጦር አዛዥ የነበረው የሩዶልፍ ግራዚያኒ ሐውልት መሰራትን በመቃወም ስድስት ኪሎ የካቲት 12 አደባባይ በወጡ ዜጎች ላይ የወያኔ ዘረኛና ሀገር በታኝ ቡድን በወሰደው እርምጃ ቁጥራቸው የበዙ ዜጎች ክፉኛ መጎዳታቸው ታውቆዋል::*

*ከ75 ዓመት ከፊት በዚሁ በስደስት ኪሎ የካቲት 12 አደባባይ ላይ የጣሊያኑ ፋሽሽት ጦር አዛዥ ግራዚያኒ ከ30 ሺህ በላይ እናትና አባቶቻችንን በጅምላ ሰብስቦ በቦምብ የፈጀና በጥይት እየጠበሰ ያቃጠለውን በሀገሩ ኢጣሊያ ሀውልት እና መናፈሻ መሰራቱን ተከትሎ ለመቃወም በወጡ ዜጎች ላይ ሀገር በቀሉ ፋሽሽቱ የወያኔ ቡድን ከፍተኛ ግፍ እና በደል እንደፈጸመባቸው የጉዳቱ ሰለባ የሆኑ ዜጎች ተናግረዋል::*

*የተቃውሞ ሰልፉን ለማድረግ የሰማያዊ ፓርቲ...ከወያኔ ወጣት ፎረም እራሳቸውን አግልለው በወጡ የተቋቋቁዋመው የባለራዕይ ወጣቶች ማሕበርና የኢትዮጵያ ሕዝብ ተቆርቆዋሪ የግል ተነሳሽ ኮሚቴ በጥምረት ያዘጋጁት ሲሆን የወያኔ ቡድን ህጋዊ መንገድ ተከትለው የተንቀሳቀሱትን አካላት ህገ ወጥ ናችሁ በሚል ሞባይላቸውን ከመንጠቅ አልፎ በጥፊና በእርግጫ እስከ መደብደብ መደረሱን በስፍራው ከነበሩ ሰዎች የደረሰን ጥቆማ ገልጾ አንድ የህወሀት ሰው እንደሆነ የተነገረለት ተክላይ የተባለ የደህንነት ባለስልጣን ፍጹም ኢትዮጵያዊነት በጎደለው ቁዋንቁዋ እየተሳደበ ታዋቂና እድሜ ጠገብ የሆኑ አዛውንቶችን በእርግጫ እየመታና ምራቅ እየተፋባቸው መኪና ውስጥ ሲከታቸው መታየቱን ከስፍራው የደረሰን ጥቆማ አጋልጦዋል::*

*በደህንነት ባለስልጣኑ ስድብና እርግጫ የተጀመረው እንግልት የፌዴራል ፖሊስ በሶስት መኪና አምጥተው አፈሳ ያደረጉ ሲሆን በግዳጅ ታፍሰው የተወሰዱት ታዋቂ ሰዎች እና በተቃውሞ ሰልፉ ላይ የተገኙ ወጣቶች ሰሜን ሆቲል አቅራቢያ በሚገኘው የአዲስ አበባ ፖሊስ እስር ቤት አስገብተው ከአንድ ሰዓት ቆይታ በሁዋላ ደግሞ ገዳም ሰፈር ወደሚገኘው አራዳ ክፍለ ከተማ ፖሊስ መምሪያ የወሰዱዋቸውና ቃላቸውን የተቀበሉዋቸው መሆኑ ታውቆዋል::*

*ወደ ቀጨኔ መድሀኒዓለም በሚወስደው መንገድ ላይ ችሎት ተብሎ በሚጠራው ሰፈር ባለ እስር ቤት በአንድ ጠባብ ክፍል ውስጥ ከ30 በላይ እስረኞች እንዲታጎሩ ተደርጎ የሰው ልጅ ከእንስሳ ባልተሻለ ሁኔታ ታሽጎ የታየበት እንደነበር እስረኞቹ ገልጸው በግዳጅ ታፍሰው ከተያዙበት ከስድስት ኪሎ የካቲት 12 አደባባይ ጀምሮ እስከ አደሩበት እስር ቤት ድረስ ከአራት ግዜ በላይ ቃላቸውን እንዲሰጡ ከመደረጋቸውም በተጨማሪ ሁሉም የእጅ ሞባይላቸውንና የአንገት ሀብሎቻቸው እንደተወሰዱባቸው ተናግረዋል::*

*ለግራዚያኒ ጥብቅና የቆመው የሀገር ውስጡ ፋሽሽት .....ግራ የተጋባው እና በፍርሀት ተውጦ ያለው የወያኔ ቡድን በማግስቱ ሰኞ መጋቢት 9 ቀን 2005 ዓ.ም ታሳሪዎቹ በቀበሌ መታወቂያ እንዲፈቱ ማድረጉ ታውቆዋል::*

በመጨረሻም ከአንድ ዓመት በፊት የተጀመረው የሙስሊሙ ማሕበረሰብ ተቃውሞ ከግዜ ወደ ግዜ እየሰፋ መጥቶ በሻሸመኔና አዳማ በዓይነቱ ልዩ የሆነ ተቃውሞ ሲያስተጋቡ መዋላቸው ታወቀ::

የአዲስ አበባ ህዝበ ሙስሊም አልቀበል ያላቸው የወያኔ ሹመኛ መጅሊሶች ወደ ደቡብ አዋሳና ሻሸመኔ በማቅናት ድጋፍ ለማግኘት ሙከራ ያደረጉ ቢሆንም ከመዲናይቱ በበለጠ ሁኔታ ከፍተኛ ተቃውሞ እንደቀረበባቸው ለማወቅ ተችሎዋል::

በዶ/ር ኪያር በተባለው አዲሱ የወያኔ ተላላኪ ሹመኛ የተመራው መጅሊስ ሕዝበ ሙስሊሙን በገንዘብ እና በጥቅማ ጥቅሞች ለማታለል በሻሸመኔ ከተማ ለ7 ቀን ፕሮግራም ይዞ የነበረ ቢሆንም ሙስሊሙ በወሰደው ቆራጥ አቋዋም በአንድ ቀን ብቻ ሊቋዋረጥ የቻለ ሲሆን ዓርብ ዕለትም በሻሸመኔ አራዳ መስጊድ በተደረገ ተቃውሞ የታሰሩት የሙስሊም መፍትሄ አፈላላጊ ኮሚቴ አባሎች በአስቸኳዋይ ይፈቱ...ተመረጡ የተባሉት አዲሶቹ አመራሮች አይወክሉንም..... አሕባሽ የተባለው የወያኔ ፖለቲካ ነው .....ጥያቄያችን በሰላማዊ መንገድ ይመለስ ሲሉ ተቃውሞ ማሰማታቸው ታውቆዋል::

በሕዝበ ሙስሊሙ ተቃውሞ የተበሳጩት የወያኔ ሹመኛ አመራሮች ለፌዴራል ፖሊስ ባስተላለፉት ትዕዛዝ መሰረት አራዳ መስጊድ ተሰባስቦ የነበረው ሙስሊም ሕዝብ ላይ የዱላ ውርጅብኝ በማዝነብ ከፍተኛ ጉዳት ያደረሱ ሲሆን ሴትዋ ማህጸንዋን ወንዱን ብልቱን እየቀጠቀጡ ለከፋ አደጋ መዳረጋቸው ታውቆዋል::

ከማይወክለን መጅሊስ ጋር አንነጋገርም በማለት ተቃውሞ ያሰሙት የሻሸመኔ ሙስሊሞች ዓርብ ዕለት መጋቢት 6 ቀን 2005 ዓ.ም በአራዳ መስጊድ የሶላት ስነ ስርዓት ከጨረሱ በሁዋላ ባሉበት ሆነው እጃቸውን ወደ ላይ እያወጡ ወያኔን ሲያወግዙ በነበረበት ወቅት የፌዴራል ፖሊስ እና የሙስሊም ቆብ የደፉ ደህንነቶች ግንቡን ዘልለው በመግባት ድብደባ መፈጸማቸውን የጠቆመው የደረሰን ዘገባ ከሻሸመኔ ከተማ እንዳይወጡ ከ81 ማዞሪያ እስከ አቦስቶ መንገድ ድረስ ተወጥሮ እንደዋለም ከስፍራው የደረሰን ጥቆማ ገልጾዋል::

ድብደባና እንግልት ከደረሰባቸው ዜጎች በተጨማሪ ከ15 ያላነሱ ወጣቶች ቀስቃሽ ናቸው ተብለው ታፍነው ወዳልታወቀ ስፍራ መወሰዳቸውንም ይሄው የደረሰን ጥቆማ ጨምሮ ገልጾዋል::

በአዳማ ከተማም በተመሳሳይ ሁኔታ ሕዝበ ሙስሊሙ ከሶላት ስነስርዓት በሁዋላ ተቃውሞ በማሰማት ላይ እንዳለ የኦሮሚያ ፈጥኖ ደራሽ እና የፌዴራል ፖሊስ በጥምረት ወደ አቡበከር መስጊድ በመግባት ከፍተኛ ድብደባ የፈጸሙ ሲሆን 12 የአዳማ ዩኒቨርስቲ ሙስሊም ተማሪዎችን አፍነው ወዳልታወቀ ስፍራ መውሰዳቸውንም ከስፍራው የደረሰን ጥቆማ ገልጾዋል::